# ስብሃት ነጋ - ከታሪክ ጋር የተጣላ ሰው

ከኢትዮሚድያ - ስብሃት ነጋ የጫካው የወያኔ አመራር ቁንጮ አባል እያለ "የሥለላ እና ባዶ ስድስት" ተብሎ የሚታወቀው የቶርቸር እና ግድያ ክፍል ኃላፊ ነበር። የብዙ እስር ቤቶች ኃላፊ! "ስብሃት ሌሊት ከመጣ፣ ለሞት ተዘጋጅተን እንጠብቃለን። ብዙ እስረኞች ተጠርተው ይወጡና በዛው ይቀራሉ" ያለን አንድ የቀድሞ የ 06 ታሳሪ ነው። አንድ ጊዜ ስብሃት ወጣት ታጋዮችን "ቤተሰብ የናፈቃችሁ መሄድ ስለሚፈቀድላችሁ እጃችሁን አውጡ!" ይላቸዋል። በጊዜው የበረሃ ኑሮ፤ ውጣ ውረዱ፣ ረሀቡ፣ ጥማቱ እና የእናት ናፍቆት ያልቻሉ ለጋ ወጣቶች ጥያቄውን ተቀብለው ቤተሰብ ጠይቀው ለመመለስ ዕድል አገኘን ብለው ከየምድባቸው ፈቃደኛ ሁነው ይቀርባሉ። የ15 እና የ16 አመት ለጋ ወጣቶች የሚገኙባቸው ከ60 በላይ ተሰበሰቡ። ስብሃት ነጋ የ"እናቴ ናፈቅሽኝ" ጉጅሌ ይህ ነው ብሎ ሳቀ። የሞት ፍርድ መሆኑ ነው። ሌሊቱም ሁሉንም በልቷቸው አደረ! (ዋቢ - ገ/መድህን አርአያ እና ተስፋይ አፅብሃ በቃልና በፅሁፍ እንደገለፁት)። ስብሃት ነጋ የፈጸማቸው ወንጀሎች ሌላ ጊዜ እንመለስበታለን። በሀገራችን "አቦይ" የሚል ቃል በጣም ክቡር ቃል ነው። አንቱታን ላተረፉ፣ ከቤተሰብ እስከ ህብረተሰብ በቅንነት ላገለገሉ አዛውንቶች የሚሰጥ ልማዳዊ ማእረግ ነው ሰዎችን እንደከብት ሲያርድ ለኖረ ጭራቅ አይገባም። ስብሃት ነጋን "አቦይ ስብሃት" ተብሎ ሲጠራ ስንሰማ ይሰቀጥጠናል። ሰይጣን ሰውን ያሳስታል፣ ስብሃት ነጋ ደግሞ ሰይጣንም ሳይቀር ያሳስታል ያሉት ማን ነበሩ? እናም "አቦይ" የምትለውን ክቡር ቃል ከዚህ በታች ከሰፈረው ድንቅ ፅሁፍ አውጥተናታል። መልካም ንባብ!

*****************

> ባሜሪካ ድምጽ ሬድዮ ማለትም በትግርኛው ክፍል [በጥር27፣2012 [አርብ]] በቀረበው ያቶ ብስራት አማረ መጽሃፍ ውይይት ዶ/ር አረጋዊ የህወሓት መስራችና አቶ ስብሃት ነጋ በሰጡት አስተያየት የሚመለከት ነው። በጸሃፊው እምነት በዚሁ ውይይት የአቶ ስብሃት አስተያየት በጣም አደገኛና ከፋፋይ መልእክት ላድማጭ አስተላልፈዋል የሚል እምነት አለው። በኢትዮጵያ ያለው ሁኔታ አነሰና በትግራይም ያንን የመከፋፈል ስሜት እንዲያብብ/እንዲሰፍን ሆን ተብሎ የተተፋ መርዝ ስለሆነ ከታሪክና ከሰውየው ባህርይ ምን ማለት እንደሆነ እንደሚከተለው ላንባቢ አቅርበነዋል። የከፋፋይነትን ቆፍጣና ባህርይ የተላበሱ አቶ ስብሃት ያሉትን ቃል በቃል በትግርኛ አስቀምጠን ወደ አማርኛ መልሰነዋል።

አቶ ስብሃት የሚከተለው በትግርኛ ብለዋል፡

***[ሕዚ ምስቲ መጽሃፍ ዝጸሃፎ ኢታአሳሲርካ ድዩ ዝሬኤ፤ ዝገደፎ ነገር ክህሉ እዩ። ነቲ ፅሁፍ ግን ከም ባከግራውንድ[background] መጠን ማለት ካብ ትግራይ ወፃኢ ካብ ኤርትራ ወፃኢ ንኻልእ ከምዘልአልካዮ፤ ንጋምቤላ፣ ንኻልዕ ዝሓውስ ኢይኮነን አክሱም። ትግራይ እውን ሙሉእ ትግራይ ዝሓውስ ኢይመስለንን። ተምብየን አካል ናይ አክሱማይት ኢምፓየር ዶ ነይሩ ዝብል ሕቶ አለኒ። ኢቨን[even] ዓጋመ ነይሩ ዶ? አብ ሓደ ኢጋጣሚ ፐረፕለስ ኦፍ ዘ ኤረትርያን ሲ ዝብል ናይ ዓጋመ ስያሞ ዝብል አብኡ ሪኤ፤ ስያሞ አበይ እዩ እንተበልኩ ዓጋመ እዩ ኢሎምዎ በቲ ናይ ቀደም አፀዋውዓ ንሱውን ፓርት ኦፍ አክሱማይት ከምዘይነበረ እየ ተረዲአ፤ ዘርፎር[therefore] ለጀንድ[legend][ፅውፅዋይ] እንተዘይኮይኑ ኮንክሪት[concrete] ዝተቀመጠ ታሪኽ ስለዘይፈልጥ ነታ መጽሃፍ ግን ኢይ ቲንክ [I think]ረለቫንት[relevant] መእተዊ ዝብል አለኒ፤ ናይ ኢትዮጵያ ታሪኽ እንደገና ክጸሓፍ ከምዘሎ እየ ዝአምን። ሓቀኛ ናይ ኢትይጵያ ታሪኽ ንኽፀሓፍ በሪ ትኸፍት ]***

**አቶ ስብሃት ያሉት ወደ አማርኛ ሲመለስ፡-**

**[አሁን ይህ የሚታየው ክፃፈው መፅሃፍ ተዛምዶ ነው። የተወው ነገር ሊኖር ይችላል። ይህ ጽሁፍ እንደ መነሻ መጠን ማለትም ከትግራይና ኤርትራ ውጭ ልክ አንተም እንዳነሳኸው ጋምቤላና ሌላም የሚጨምር አይደለም አክሱም። ወደ ትግራይም ስንመጣ አሁን ያለው ትግራይን የሚጨምር አይመስለኝም። ተምቤን የአክሱማይት ኢምፓየር አካል ነበር ወይ የሚል ጥያቄ አለኝ። እንዲያውም ኢጋሜስ[አውራጃ] ነበር ወይ? ባንድ ኢጋጣሚ በፐረፐለስ ኦፍ ኤርትራ የኢጋሜ ስያሞ የሚል አየሁ። ስያሞ ማለት ደግሞ ብድሮ ኣጠራር ኢጋሜ ነው ብለውታል።እና የአክሱም አካል እንዳልሆነ ተገነዘብኩኝ። እና አፈ-ታሪክ ካልሆነ የተጨበጠ ታሪክ ስልማላውቅ ስለ መፅሃፍዋ ግን እንደማስበው ተገቢ መንደርደርያ ነው እላለሁ። የኢትዮጵያ ታሪክ እንደገና መጻፍ አለበት ብዬ ነው የማምነው። እውነተኛ ታሪክ እንዲፃፍ[መፅሃፍዋ] በር ትከፍታለች።]**

የአቶ ስብሃት አስተያየት የመጣው በመጀመርያ ዶ/ር አረጋዊ ያክሱም መንግስት [ኢምፓየር] ታሪክ ሰፊ ግዛት የሚያጠቃልል እንደነበረና [ሲዳሞን ሜጫንና እናርያ በደቡብ በሰሜን ደግሞ ሜሮዌን[ ከሱዳን ዋና ከተማ በሰሜናዊ ምስራቅ 135 ማይልስ ርቃ የምትገኝ ያክሱም አካል የነበረ ታሪካዊ ቦታ] እንዲሁም እስከ ቀይ ባህር ጠረፍ ድረስ እንደነበረ ከገለጹ በኋላ ነው። ታሪክም ዶ/ር አረጋዊን ያሉትን ይላል፤ ይደግፋቸዋልም።

ስብሃት ግን ያክሱም መንግስት በዶ/ር አረጋዊ ከተባለው በተቃራኒ በመቆም እንድያውም ትግራይን በሙሉ ማካተቱ እንደሚጠራጠሩ ነግረውናል። ለጥርጣርያቸው መንስኤ የሆነውም እንደ ማስረጃ የጠቀሱት ቢኖር *Periplus of the*

*Erythraean Sea* [ፐሪፐለስ ኦፍ ዘ ኤርትርያን ሲ] የሚል ግሪኮች ድሮ ስለ ጉዞና የንግድ ሁኔታ የሚተርክ ጽሁፍ ጠቅሰዋል። ይህ ጽሁፍ እሳቸው ላሉት በትኛው ገጽ እንደሚገኝ ግን አልተናገሩም።

ባቶ ስብሃት የተጠቀሰው የታሪክ አስረጅ ግን ስለ አክሱም ሲናገር እንደ ሚከተለው ይላል፡

> [The first mention of Aksum was in a Greek guidebook written around A.D. 100, *Periplus of the Erythraean Sea*. It describes Zoskales (ZAHS•kuh•leez), thought to be the first king of Aksum. He was "a stickler about his possessions and always [greedy] for getting more, but in other respects a fine person and well versed in reading and writing Greek." Under Zoskales and other rulers, Aksum seized areas along the Red Sea and the Blue Nile in Africa. The rulers also crossed the Red Sea and took control of lands on the southwestern Arabian Peninsula.]

[ http://sharepoint.chiles.leon.k12.fl.us/mcneilt/Textbook%20for%20World%20History/Chapter%2008/Ch%208%20Sec%203.pdf

ትርጉሙ፡
[ስለ አክሱም ለመጀመርያ ጊዜ ተጽፎ የተገኘው በ100 ዓ.ም. አካባቢ *በፐሪፐለስ ኦፍ ዘ ኤርትርያ ሲ* የተባለ መጽሃፍ ነው። የሚገልጸውም ስለ ዘስካለስ የተባለው የመጀመርያው ያክሱም ንጉስ ነው። ንጉሱ በንብረቱ በጣም ጠንቃቃና ለመጨመርም ከፍ ያለ ፍላጎት የነበረው ንጉስ ነው። በሌላ ጎኑ ደግሞ ጥሩ ሰውና እንዲሁም የግሪክ ቋንቋ አቀላጥፎ የሚናገርና የሚጽፍ ነበር። ***<u>አክሱም በዘስካለስና ሌሎች ገዢዎች በነበሩበት ሰዓት ቀይ ባህርና የጥቁር አባይ አካባቢ ግዛትዋ ነበር</u>***። ገዢዎቹ ወደ ደቡብ አረብያ[የመን] በመሻገርም የተወሰኑ መሬቶች በቁጥጥራቸው አርገው ነበር።]

ቁም ነገሩ በግልጽና በማያሻማ መንገድ ያክሱም ስልጣኔ ጥቁር አባይንም ጭምር እንደሚጠቀልል ይገልጻል። እና የአቶ ስብሃት አባባል ከየት እንዳመጡት ግልጽ አይደለም ሙግታቸውም ውሃ አያቋጥርም እንላለን።

እስኪ ደግሞ ያገራችን ምሁራንና ትላልቅ ሰዎች ስለ አክሱም ያሉትን እንመልከት፡

ዶ/ር ተወልደ ትኩእ ባዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የጥናትና ምርምር አባል እንዲሁም የታሪክ ተማራማሪ የሆኑት መጽሃፋቸው ከዶ/ር አረጋዊ አባባል ጋር ይስማማል። አብነቶችን ብናስቀምጥ ለተባለው እንደ ማስረጃ ያገለግላል። ***የኢትዮጵያ አንድነት እና ኢጣልያ*** በሚለው መጽሃፋቸው [ዶ/ር ተወልደ ትኩእ የታሪክ ምሁር] ስለ አክሱም ያሉትን እንይ፡

"የአክሱም ታሪክ የምናውቀው ከመጀምርያ ሲቋቋም አይደለም። በጠፋው የአዱሊስ ሓወልት የምናገኘው ጽሁፍ ያንድ አዲስ መንግስት ሳይሆን የአንድ ረጅም ታሪክ ያሳለፈ የብዙ ሺ የሚቆጠሩ አመታት የተደራጀ የምድር ጦርና የባህር ሃይል ያለው ከታላቁ የሮማ መንግስት በጦር ሜዳ የሚፋለም መንግስት ነው። ንጉሱ የሚተርከው [በሃወልቱ ያለው ጽሁፍ ማለት ነው] በሃገር ውስጥና በውጭ ሃገር ስላደረጋቸው ዘመቻዎች ነው"[ገጽ 38] ይላል

በመቀጠለም የታሪክ ምሁሩ ስለ አክሱም ታላቅነትና ገናናት እንዲሁም ወደ የመን የተደረገው ዘመቻ ሲገልጹ፡

"ዘመቻው ግዙፍ ነበር። የኢትዮጵያ ወታደሮች ቀይ ባህርን ሲያቋርጡ በ191 በቢዛንታይን የንግድ መርከቦችና በ170 አጼ ካሌብ ባሰራቸው ተሳፍረው ነበር። የመን የደረሱትንና አጼ ካሌብ ያካሄደው ዘመቻ በሁለት ዙር ነበር"[ገጽ.47]

ግሪካዊ የታሪክ ተማራማሪ ሄሮዶቶስም ያክሱም[ኢትዮጵያ] ስልጣኔ ክነሮማና ፐርስያ እንዲሁም ቻይና ጋር የሚወዳደር ትልቅ ግዛት ያጠቃለለ እንደነበር ይገልጻል።

ንቡረዕድ ገብረመስቀል ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር ስትዋሃድ አፄ ኃ/ስላሴ ክኤርትራ ሲመለሱ እግረ መንገዳቸው ወደ አክሱም ብቅ ብለው በነበሩበት ሰአት ንቡረዕዱ ከንጉሱ ፊት ቀርበው ንግግር ሲያደርጉ ባክሱም ዘመነ መንግስት አብርሃ ትግራይን ሲገዛ ታናሽ ወንድሙ አፅብሃ ደግሞ ሸዋን ይገዛ እንደነበረና ይህ ማለት ደግሞ የትግራይና የሸዋን ትሥሥር የሚያመልክት እንደሆነ የገለጹበት ሁኔታ በዘውዴ ረታ ስለ ኤርትራ ችግር ባቀለሙት መጽሃፋቸው ተዘግቦ ይገኛል። ይህ ታሪካዊ ትስስር ሸዋ ያሉት አዛውንቶችና ትግራይ ያሉት ሽማግሌዎች አሳምረው ያውቃሉ እኛ ልጆቻቸውም ያሉትን እናምናለን።

በመጨረሻም የማያዳግም ማስረጃ የሚጠቀሰ ቢኖር ስለ ቅዱስ ያሬድ ነው። የነበረበት ጊዜ ባጼ ገብረ መስቀል በ6ኛው ክ/ዘመን ነው። ያሬድ ያክሱም ተወላጅ ይሁን እንጂ መጨርሻ አካባቢ ወደ ጎንደር አካባቢ በመሄድ ነው መንፈሳዊ ጊዜው ያሳለፈው። ጸናጽልና መቆምያው በጣና ጭርቆስ ቤተ ክርስትያን[በጎጃም] እስከ አሁን ድረስ እንዳሉ ይነገራል። ታድያ አቶ ስብሃት የአክሱም 'ኢምፓየር' መላ ትግራይን ማካለሉ እንጂ ማለታቸው ከምን የመነጨ ነው ትላለህ/ትያለሽ አንባቢ?

በታሪክ ታላላቅ መንግስታት[ኢምፓየር] የምንላቸው ትልቅ የሆኑበት ምክንያትና ባህርይ[ክራተርያ] መሰረቱ ሰፊ ግዛትና ሃብት ነው። ይህ ማለት ደግሞ ብዙ ህዝብና ሪሶርስ በጃቸው ካስገቡ በሃላ ነው ማለት ነው። የአክሱም ስልጣኔም ይህንኑ መስፈርት ይጋራል/ያሟላል። ከዚሁ ባህርይ ውጭ ሊሆንም አይችልም።

እንግዲህ አንባቢ/አንባቢት ያገርና የውጭ የታሪክ ምሁራን ስለ አክሱም ከላይ የተጠቀሰውን ይላሉ፤ አቶ ስብሃት ግን የፖለቲካ እንጂ የታሪክ ምሁር ያልሆኑ አዛውንት ያክሱም ስልስጣኔ ላለው ኢትዮጵያስ ይቅርና መላ ትግራይን ማዳረሱ እጠራጠራለሁ ብለው መናገራቸው ምን  ለማለት ፈልገው ነው? ነገሩ አስገራሚ ወይስ አሳዛኝ?

ያቶ ስብሃት መልእክት ትግራይን ለሁለት የሚከፍል ንግግር ነው ካንደበታቸው ሲነገሩን የሰማነው። ይህ አስተያየት በተራ ሰው አንደበት የተነገረ ሳይሆን ካንድ ቱባ የህወሓት መሪ ነው። እና ለዚሁ ሃሳብ ምን ለማለት እየተፈለገ እንደሆነ የሚሰማንን እናስቀምጥና አንባቢ ደግሞ የራሱ/የራስዋ ግንዛቤ ይወስዳል።

ስብሃት ነጋ በመጀምርያ በመምህርነት ቀጥለውም ወደ ትግል አለም ገብተው እስከ አሁን ከፖለቲካ አለም ያልተለዩ ሰው ናቸው። በትግራይ ሰው ህሊናና በታሪክ የሌለ ነገር በመገናኛ ብዙሃን ቀርበው ያክሱም ስልጣኔ ለኢትዮጵያ ታላቅዋ አገር ይቅርና ለሁሉም የትግራይ አውራጃዎች እንኳ የሚመለከት አልነበረም [አጋሜና ተምብየን እንደማያካትት] ወይም ጥርጣሬ እንዳላቸው ሲገልጹ የሰማናቸው በሃዘን/በቁጭት ነው! ያሉበትን ድርጅት በባህላችንና ሃይማኖታችን ያሳደረው አሉታዊ ተጽእኖ አነሰና ነው አሁን በቀረችው አንድነታችን የመጡብን? ያስብላል።

አቶ ስብሃት! ለመሆኑ ምን ያህል ስለ ኢትዮጵያ ታሪክ የተጻፉ መጻህፍቶች አንብበው ነው አሁን ወደአሉን ጥርጣሬ ሊገቡ የቻሉት? ። ቁንጽል ስለ ፐረፕለስ ኦፍ ዘ ኢርትራን ሲ የሚል ዋቢ ብቻ በማስቀመጥ ስለ ኢጋሜ አውራጃ ያክሱም ስልጣኔ አካል እንዳልነበረ ሊነግሩን ሞክረዋል። ታድያ ለታሪክ ሰዎችና ለኛ እስከ አሁን ያልተገለጸልን ምስጢር ለርስዎ እንዴት እንደበራላቸው ለወደፊት ዘርዝረው ቢነግሩን መልካም ነበር። ያወቅነው ነገር ቢኖር ግን የታሪክ እውቀትዎ አንሶ ሳይሆን ሆን ብለው ታሪካችንን እየበለዙ ነው የሚለው ላሉት ነውረኛ አባባል ይገልጸዋል።ጉዳዩ ቅድም እንደጠቀስነው ተራ ንግግር/አስተያየት አይደለም፡፡ እስኪ ስለ አቶ ስብሃት ጸባይና ተግባር የሚነገሩትን [ከዚሁ በታች ያሉትን] አንባቢ/አንባቢት ልብ እንዲለውና አሁን ሰውየው ካሉት አያይዞ እንዲመዝነው በትህትና እንጠይቃለን።

> ***ሰውየው ካውራጃ አልፈው ወደ ሲጋ ዝምድና ወርደው የማዳላት ስራ ይተገብራሉ። የስራ ዕድልና ሹመት ሲሰጡ ባቶ ስብሃት ቤት ዋና መለኪያው እውቀትና ችሎታ ሳይሆን እሳቸው ከተወለዱበት/ከተማሩበት አካባብን መሰረት አድረገው እንደሚሰሩ ነው።***

እንግዲህ ትክክለኛውን ታሪካችንን ባልሆነ ይትበሃል[ተረት ተረት] ነገር ለመተካት የቃጡ ደፋር አዛውንት ከላይ የተጠቀሰውን የማይደገፍ ባህርይና ተግባር ባለቤት ለመሆን ምን ሊያግዳቸው ይችላል?

በትንሽ ግዛት የተከለለ ህብረተሰብ ማለትም ባቶ ስብሃት አባባል ባክሱም ባድዋና በደቡብ ኤርትራ[አከለጉዛይና ሰራዬ] በነበሩት ህዝቦችና ሃብት ብቻ ያክሱምን ስልጣኔ የሚያክል ታሪክና መንግስት ሊፈጥሩ ከቶ አይቻላቸውም። ከሎጂክም ውጭ ነው። ማለትም ኢምፓየር ከሚለው ባህርይ ራሱ የሚጋጭ አስተሳሰብ ነው።በቅርቡ ታሪክ እንኳ ስንመለከት እንግሊዝ ትልቅ የሆነችበት ምክንያት ያለምን ሩብ አካል ስለገዛችና የተገዢዎቹ ሃብት በመበዝበዝዋ ነው። አሜርካን ብንመለከት ሰፊ ግዛትና ሃብት ነው ትልቅ ያደረጋት እንጅ ሌላ ምስጢር አይደለም።አክሱም በራሱ ትልቅ ስልጣኔ የነበረና ግዛቱም ሰፊ እንደነበረ ካለው ቅርስና ከተጻፈው ታሪክ መናገር ይቻላል። የቆሙት ሃወልቶችና የተሰሩት ጥበቦች እንዲሁም የወረስነው ፊደል በቁጥር አነስተኛ ህዝቦችና በጠባብ ግዛት በሰፈሩ ህዝቦች የተገነቡ ሳይሆኑ የብዙ ህዝብ ጉልበትና ሃብት ውጤት መሆናቸው ግልፅ ነው።
ከላይ የተገለጸው ሃይለ ሃሳብ የሚደግፍ አስረጅ ደግሞ እስኪ እንይ፡

**የኢትዮጵያ ሥልጣኔ መነሻው፥ ጉዞውና መድረሻው** በሚል ርዕስ የተከተበው ጽሁፍ በታሪክ ምሁር የሆኑ ኢትዮጵያዊ ፐ/ር ጌታቸው ኃይሌ እንደሚከተለው ይላል፡

*"የዓባይን ግልገልነትና ዓቢይነት ያነሣሁት ለሥልጣኔያችን ልደትና እድገት ምሳሌ እንዲሆነኝ ነው። የኢትዮጵያ መንግሥት ይዞት የሚጓዘው ሥልጣኔ የተወለደው የኢትዮጵያ መንግሥት እተወለደበት ቦታ ነው፤ ጽራዕ ወይም ትግራይ ውስጥ ማለቴ ነው። ሥልጣኔው በዚያና በዚህ ተጒዞ፥ ተጒዞ እየዳበረ መንግሥታዊ ማእከላችንን አዲስ አበባ ላይ ካደረግነው ከእኛ ዘመን ደርሷል። የዓባይ ወንዝ ሲጓዝ ከየቦታው የሌላ ወንዞች ውኻ እየተመገበ እንደገዘፈ ሁሉ፥ የኢትዮጵያ ሥልጣኔም መንግሥት እጁን ከዘረጋበትና ማእከሉ ካደረገበት ቦታ ሁሉ ምግብ እያገኘ ገዝፏል። መግዘፍ ብቻ ሳይሆን መልኩም በመጠኑም ቢሆን ተለውጧል።"*http://ethiomedia.com/broad/ethiopian_civilization.pdf

እና እነ ካሌብ እስከ የመን ድረስ ዘምተዋል ተብሎ የተጻፈው ታሪክና ያቶ ስብሃት ነጋ ደግሞ ኢጋሜና ተምብየን ያክሱም አካል ነበሩ ለማለት ያስቸግራል የሚለው መሰርይ አስተሳሰብ በራሱ አይጋጭም ወይ? በዚሁ ያልገባን ቢኖርና የምንጠይቀው በወቅቱ በኢጋሜና በተምብየን አካባቢ ሰው አልነበረም ነው? ወይስ ነበሩ ግን ለብቻቸው መንግስትና ታሪክ ነበራቸው ለማለት ነው የተሞኮረው? ለመሆኑ አክሱም ወደቡ አዱሊስ አልነበረም ወይ? ወይስ እንደአሁኑ አክሱማውያን ወደቡ ተከራይተው ነው ሲወጡና ሲገቡ የነበሩት? ኢጋሜ ያለው ጉሎ መከዳስ የሳባ ታሪክና ያክሱም አካል አይደለምን? ባለስላጣን ሁነው በድርጅታቸው የታቀፉትን አባላት አንዱን ከፍ ሌላው ደግሞ ዝቅ የማድረግ ችሎታ ባንድ ወቅት እንደነበራቸው ይታወቃል አቶ ስብሃት። ያች የተለመደች አመልም እንግዲህ በታሪካችን ለመድገም የፈለጉ ይመስላሉ። በዚሁ ግን አዳልጦዋቸው ሲወድቁ አይተናልና፤ ለወደፊቱ ባይሞክር መልካም ነው።

ያክሱም ስልጣኔ መላ ትግራይን እንደሚጠቀልል የተጨበጠ ታሪክ የለም ብለዋል አቶ ስብሃት። ምን ያህል መጻህፍት ቢፈትሹ ነው ይህ ለማለት የደፈሩት? የተጨበጠ የለም የሚል ሰው እኮ ብዙ አንብቦና ተመራምሮ ነው እንጂ ከሜዳ ተነስቶ በስሜት የሚባል ነገር ለትዝብት ይዳርጋል። ማስረጃ የለም ማለት ያ ጉዳይ አልነበረም ማለት አይደለም። ወደ ገለጹት ጉዳይ ስንመለስ ደግሞ እኛ በምናውቀው መንገድ ያገርና የውጭ ታሪክ ፀሃፊዎች ያሉትን የሚደግፍ በብዛት ሞልተዋል። እና ምን ለማለት እንደፈለጉ እንቆቅልሽ ሳይሆን ያው ያች መርዘኛ የመከፋፈል ስራ ህይወት እንድትዘራ ስለፈለጉ እንጂ።

ስለ አክሱም ታሪክ ሲገልጹ ኣቶ ስብሃት አንድ ነገር ረስተዋል።  ማለትም ባህር የሆነውን ታሪካችን እንኳንስ በፖለቲከኛ ይህ ነው ያ ነው ሊባል ይቅርና ለታሪክ ባለሞያዎችም እስከ ዛሬ ድረስ እንቆቅልሽ ነው። በዚህ እድሜዎ ያንድ እናት ልጆች ለሁለት ለመከፋፈል የቃጡና በዚሁ አድራጎታቸው የሚታዘንባቸው ስብሃት ናቸው እንላለን። ሰው የድሜ ባለጸጋ ሲሆን ያምላክ ትዕዛዛት ያከብራል፤ ከዚያም አልፎ ለሰውም ፍቅር ይለግሳል። እርስዎ ግን የታጠቁትን ጎራዴ  ካፎቱ አውጥተው በታሪካችንና በክብራችን አንገት ላይ ለማዋል ሙከራ አድርገዋል።ማውቅ ያለብዎትን ግን እኛ የትግራይ ሰዎች/ልጆች ያንድ እናትና አባት መሆናችንና አውራጃ አጥር ሁኖ እሳቸው ወደ አዘጋጁልን አደገኛ ወጥመድ እንደማንወድቅ አሳምረን ልንነግርዎት እንፈልጋለን! ! !

ማሳሰብ የምንፈልገው አዳንድ የትግራይ ማህበር ነን ወይም የትግራይ ጉዳይ ያገባናል የሚሉ ማህበራትና ግለሰቦች እኛና እነሱ ወይም ትግራይን ለሁለት የሚከፍል አባባል ካቶ ስብሃት ሰምተዋል። እና ምን ይላሉ? በዚሁ ዙርያ የተሰማቸውን ቢገልጹልን መልካም ነው።

አቶ ስብሃት ነጋ የታሪክ ምሁር አይደሉም ግን የፖለቲካ ምንዝርና ሲፈለጉ ጎራ እንደሚልዋት አይተናል፤ ለወደፊትም ስብሃት የሚለው ስምም ፍቺው ***<u>ከፋፋይና ያክሱምን ታሪክ ለማሳነስ የሞከረ</u>*** ተብለው ታሪክ ሲያወሳቸው ይኖራል።

ሃ/ደ

<u>ዋቢ ፅሁፎች</u>

1. የኢትዮጵያ  አንድነት እና ኢጣልያ። ዶ/ር ተወልደ ትኩእ.ሚያዝያ 1990
2. ማስታወሻ[ስብሃት ገብረ እግዚአብሄር]። ከዘነበ ወላ የካቲት 1993 ገጽ 296
3. http://sharepoint.chiles.leon.k12.fl.us/mcneilt/Textbook%20for%20World%20History/Chapter%208/Ch%208%20Sec%203.pdf
4. http://ethiomedia.com/broad/ethiopian_civilization.pdf